# Meningococcal ACWY ክትባቶች—MenACWYእና MPSV4: ማወቅ የሚገባዎት

Many Vaccine information Statements are available in Spanish and other languages. See www.immunize.org/vis

Hojas de información sobre vacunas están disponibles en español y en muchos otros idiomas. Visite www.immunize.org/vis

## 1 መከተብ ለምን አስፈለገ?

Meningococcal በሽታ ከባድ ህመም ሲሆን የሚከሰተው Neisseria meningitidis በሚባል ባክቴሪያ ነው፡ ፡ ለሜኒንጃይተስ (የአእምሮ እና የህብለ ሰረሰር መስመር ኢንፌክሽን) እና ለደም ኢንፌክሽን ሊዳርግ ይችላል፡ ፡ Meningococcal በሽታ ብዙ ጊዜ ያለ ማስጠንቀቂያ ይከሰታል — ጤነኛ በሆኑ ሰዎችም ላይ ይከሰታል።

Meningococcal በሽታ ከሰው ወደ ሰው ቅርብ በሆነ ንክኪ (በማሳል ወይም በመሳሰም) ወይም በረጅም ንክኪ፣ በተለይ አንድ ቤት ውስጥ በሚኖሩ ሰዎች መሃከል ሊስፋፋ ይችላል።

“የበሽታ አይነቶች” የተባሉ 12 የተለያዩ የ N. meningitidis አይነቶች አሉ። የበሽታ አይነቶች A፣ B፣ C፣ W፣ እና Y አብዛኛውን የ meningococcal ህመም የሚፈጥሩ ናቸው።

ሁሉም ሰው የ meningococcal በሽታ ሊያዝ ይችላ ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ከሌላ በተለየ የበለጠ ስጋት ውስጥ አሉ፣ እነዚህም፡-

- ከአንድ ዓመት በላይ የሆኑ ህጻናት
- ከ 16 እስከ 23 ዓመት ውስጥ ያሉ ጎረምሶችና ወጣቶች
- የሰውነት የመከላከል አቅምን የሚጎዳ በሽታ ታማሚዎች
- ከ N. meningitidis ጋር ተለይተው የሚሰሩ ማይክሮ ባዮሎጂስቶች
- በወረርሽኝ ጊዜ ስጋት ውስጥ ያሉ ሰዎች

በህክምና ላይም እንኳን እያለ፣ የ meningococcal በሽታ ከ 100 ሰዎች ውስጥ ከ 10 እስከ 15 ሰዎችን ይገድላል፡ ፡ ከተረፉት ውስጥ 100 ሰዎች ከ10 እስከ 20 ሰዎች እንደ የመስማት ችግር፣ የአእምሮ ጉዳት፣ የኩላሊት ጉዳት፣ እግር መቆረጥ፣ የነርቨስ ሲስተም ችግሮች ወይም ከቆዳ ችግር የተነሳ ጠባሳ ችግሮች ያጋጥማቸዋል።

**Meningococcal ACWY** ክትባቶች በ የበሽታ አይነቶች A፣ C፣ W፣ እና Y የሚከሰቱ የ meningococcal በሽታዎችን ይከላከላል። የበሽታ አይነት B ን ለመከላከል የተለየ የ meningococcal ክትባት አለ።

## 2 Meningococcal ACWY ክትባቶች

የበሽታ አይነቶች A፣ C፣ W፣ እና Y ን ለመከላል በምግብና መድኀኒት ቁጥጥር (FDA) የተፈቀዱ ሁለት አይነት የ meningococcal ክትባቶች ይገኛሉ፡ meningococcal conjugate ክትባት (**MenACWY**) እና meningococcal polysaccharide ክትባት (**MPSV4**)።

ከ 11 እስከ 18 ዓመት ዕድሜ ላይ ለሚገኙ ታዳጊዎች ሁለት የ MenACWY ክትባቶችን በተደጋጋሚ ይመከራሉ: የመጀመሪያው ክትባት ለ 11 ወይም ለ 12 ዓመት፣ ለ 16 ዓመት ደግሞ የጨመረ ክትባት። አንዳንድ ታዳጊዎች፣ HIV ያለባቸውንም ጨምሮ፣ ተጨማሪ ክትባት ማግኘት አለባቸው፡ ፡ ለበለጠ መረጃ የህክምና እንክብካቤ ሰጪዎን ያማክሩ።

ለታዳጊዎች ተደጋጋሚ ክትባት ከመስጠት በተጨማሪ፣ MenACWY ክትባት ለአንዳንድ ሰዎች መስጠት ይመከራል።

- በ የበሽታ አይነት A፣ C፣ W፣ ወይም Y meningococcal በሽታ ወረርሽኝ ጊዜ ለአደጋ የሚጋለጡ ሰዎች
- ጣፊያው የተጎዳ ወይም የተወገደ ሰው
- “Persistent complement component deficiency” በሚባል በጣም አልፎ አልፎ በሚከሰት የበሽታ መከላከል አቅም መዳከም ያለበት ሰው
- Eculizumab (ወይም Soliris®) የሚባል መድኀኒት የሚወስድ ሰው
- ከ N. meningitidis ጋር ተለይተው የሚሰሩ ማይክሮ ባዮሎጂስቶች
- ለምሳሌ እንደ አፍሪካ ውስጥ ያሉ meningococcal በሽታዎች በብዛት ወደሚገኙባቸው በታዎች መጓዝ፣ መኖር
- በኮሌጅ ማደሪያ ውስጥ የሚኖሩ አዲስ የኮሌጅ ተማሪዎች
- የአሜሪካ ውትድርና ተቀጣሪዎች

ከ 2 እስከ 23 ወር ህጻናት፣ እና የተለያየ የህክምና ችግር ያለባቸው ሰዎች በሽታውን ለመከላል በቂ የሆነ ክትባት መውሰድ አለባቸው። ምን ያህል እና በየስንት ጊዜ ክትባት እንደሚወሰድ እንዲሁም ቡስተር ክትባቶችን በተመለከተ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎን ይጠይቁ።

እድሜያቸው ከ 2 ወር እስከ 55 ዓመት ያሉና MenACWY ን ከዚህ በፊት የወሰዱ ሰዎች እንዲሁም ብዙ ክትባቶች የሚያስፈልጋቸው ከሆነ መውሰድ ያለባቸው **MenACWY** ክትባትን ነው።

ከ 55 ዓመት በላይ የሆኑ አንድ ክትባት ብቻ ለሚያስፈልጋቸው(ተጓዦች ወይም በወረርሽኝ ጊዜ) አዋቂዎች የሚመከረው **MPSV4** I ነው።



U.S. Department of Health and Human Services
Centers for Disease Control and Prevention

## 3 አንዳንድ ሰዎች ይህንን ክትባት መውሰድ የለባቸውም

ክትባቱን ለሚሰጠው ሰው መንገር ያለብዎት፡

- **ከባድና ህይወትን አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል አለርጂ ካለብዎ።**

  ከዚህ በፊት ከወሰዱት ከ meningococcal ACWY ክትባት የተነሳ ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል አለርጂ ከተነሳብዎ ወይም ከዚህ ክትባት ጋር በተያያዘ ከባድ አለርጂ አጋጥምዎ የሚያውቅ ከሆነ፣ ይህንን ክትባት አይውሰዱ። ስለ ክትባቱ ይዘቶች ክትባት ሰጪዎ ሊነግርዎት ይችላል።

- **አርጉዝ ወይም የሚያጠቡ ከሆነ።**

  ለእርጉዝ ሴት ወይም ለምታጠባ ሴት ይህ ክትባት ሊያስከትል ስለሚችለው ስጋት በቂ የሆነ መረጃ የለም። በእርግዝና ወቅት በግልጽ ከተፈለገ ብቻ መወሰድ አለበት።

እንደ ጉንፋን ያለ ብዙ የማይጎዳ ህመም የሚያምዎ ከሆነ ክትባቱን ዛሬ መውሰድ ይችላሉ። ከበድ ያለ ወይም በጣም ህመም ላይ ከሆኑ፣ እስኪሻልዎ ድረስ ይጠብቁ። ሀኪምዎ ሊያማክርዎ ይችላል።

## 4 የክትባት አለርጂ ስጋቶች

ክትባትን ጨምሮ በሁሉም መድሀኒቶች የጎንዮሽ ጉዳት የመፈጠር እድል አለ። እነዚህ መለስተኛ ሲሆኑ በትንሽ ቀናት ውስጥ በራሳቸው የሚጠፉ ናቸው፤ ነገር ግን ከባድ ህመም ሊፈጠር ይችላል።

Meningococcal ACWY ክትባትን ከሚወስዱ ሰዎች፣ ግማሽ የሚያህሉት ከክትባት በኋላ **መለስተኛ ህመም** የተወጋበት በታ ላይ መቅላት መይም መቁሰል ያጋጥማቸዋል። እነዚህ ችግሮች የሚከሰቱ ከሆነ ከ 1 እስከ 2 ቀን ይቆያሉ። ከ MPSV4 ይልቅ በ MenACWY ላይ በተደጋጋሚ ይከሰታሉ።

ክትባቱን ከሚወስዱት ውስጥ ትንሽ መቶኛ የሚሆኑት መለስተኛ ትኩሳት ያጋጥማቸዋል።

**የትኛውንም ክትባት ከወሰዱ በኋላ የሚያጋጥሙ ችግሮች፡**

- ከህክምና በኋላ፣ ክትባትን ጨምሮ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ራሳቸውን ይስታሉ። ለ15 ደቂቃ መቀመጥ ወይም መተኛት ራስን መሳት እንዲሁም በመውደቅ የሚመጣውን ጉዳት ይከላከላል። የድንዛዜ ስሜት፣ የእይታ ለውጥ ወይም ጆሮ ውስጥ ማቃጨል ከተሰማዎት ለሀኪምዎ ይንገሩ።
- አንዳንድ ሰዎች ትከሻ ላይ ከበድ ያለ ህመም ሲሰማቸው የተወጉበት አጃቸውን ማንቀሳቀስ ያስቸግራቸዋል። ይህ አልፎ አልፎ የሚከሰት ነው።
- የትኛውም መድኃኒት ከበድ ያለ የአለርጂክ ሊያስነሳ ይችላል፡ ፡ ከክትባት የሚመጡ አለርጂኮች በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ሲሆኑ  ከ አንድ ሚሊዮን ክትባቶች በ1 ይገመታል እናም ከክትባት ጊዜ በትንሽ ሰዓት ውስጥ ይጀምራሉ።

ልክ እንደ ሌላው መድኃኒት፣ ክትባት በጣም ከባድ ጉዳት ወይም ሞት የሚያስከስትበት በጣም ጠባብ እድል አለ።

የክትባቶች ደህንነት ሁልጊዜ በቅርብ ክትትል ውሰጥ ነው። ለበለጠ መረጃ ይህን ይጎብኙ፡ **www.cdc.gov/vaccinesafety**/

## 5 አደገኛ የሆነ የአለርጂ ምልክት ቢኖርስ?

**ማየት ያለብኝ ምንድነው?**

- ስጋት የሆንዎበትን ነገር እንደ ከባድ የአለርጂክ ምልክት፣ ከፍተኛ ትኩሳት ወይም ያልተለመዱ ባህርያትን ይመልከቱ።

  የከባድ አለርጂክ ምልክቶች የሚያካትቱት ሽፍታዎች፣ የፊትና የጉሮሮ እብጠት፣ የመተንፈስ ችግር፣ ፈጣን የሆነ የልብ ምት፣ መደንዘዝ እና ድካም ናቸው—አብዛኛውን ጊዜ ከክትባት በኋላ ከትንሽ ደቂቃ እስከ ትንሽ ሰዓታት ይፈጠራሉ።

**ምን ማድረግ አለብኝ?**

- ከባድ የሆነ የአለርጂክ ምልክት ወይም ሊቆይ የማይችል አስቸኳይ ከመሰለዎት 9-1-1 በመደወል አቅራቢያ ወዳለው ሆስፒታል ይሂዱ። ካለበለዚያ ሀኪምዎ ጋር ይደውሉ።
- ከዚያ በኋላ የአለርጂው ምልክት ለ "Vaccine Adverse Event Reporting System" (VAERS) ሪፖርት መደረግ አለበት። ሃኪምዎ ይህንን ፋይል ሪፖርት ማድረግ አለበት ወይም እርስዎ ራስዎ የ VAERS ድረ ገጽን በ **www.vaers.hhs.gov**, በመጠቀም ወይም በ **1-800-822-7967**መደወል ይችላሉ።

VAERS የህክምና ምክር አይሰጥም።

## 6 The National Vaccine Injury Compensation Program

የ National Vaccine Injury Compensation Program (VICP) የፌደራል ፕሮግራም ሲሆን በክትባት ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ካሳ የሚሰጥ ነው።

በክትባት ጉዳት እንደደረሰባቸው የሚያስቡ ሰዎች ስለ ፕሮግራሙ ለማወቅ እና መጠየቂያ ለመሙላት በ **1-800-338-2382** ይደውሉ ወይም የ VICP ድረ ገጽን በ **ይጎብኙ**። የካሳ ጥያቄ ለመጠየቅ የጊዜ ገደብ አለው።

## 7 እንዴት የበለጠ ማወቅ እችላለሁ?

- የጤና እንክብካቤ ሰጪዎን ይጠይቁ። እርሱ ወይም እርሷ የክትባቱን ማብራሪያ ወረቀት ወይም ሌላ የመረጃ ምንጭን መጠቆም ይችላል/ትችላለች።
- የእርስዎን ግዛት የጤና ዲፓርትመንት ጋር ይደውሉ።
- Centers for Disease Control and Prevention (CDC) ን ያግኙ፡
  - **1-800-232-4636** (**1-800-CDC-INFO**) ይደውሉ ወይም
  - የ CDC ን ድረ ገጽ በ **ይጎብኙ**

---

Vaccine Information Statement

Meningococcal ACWY Vaccines - Amharic

Office Use Only

03/31/2016

42 U.S.C. § 300aa-26

Translation provided by Minnesota Department of Health